


# እግዚአብሔር

መሰረታዊ አስተምሮዉን ባልቀየረ መልኩ ይህንን ትምህርት በማንኛዉም ዓይነት መንገድ ለሌላዉ በማዳረስ በአገልግሎቱ ይሳተፉ።

---

እግዚአብሔር...

በአንድነት፥ በሦስትነት የሚሰለስ የሚቀደስም የዘላለም አምላክ ነው። እንደ አዳም አንድ ፤ እንደ አብርሃም ፥ ይስሃቅ ፥ ያዕቆብም ሦስት አይደለም፤ አንድ ሲሆን ሦስት ፤ ሦስትም ሲሆን አንድ ነው እንጂ!

መሰረታዊ አስተምሮዉን ባልቀየረ መልኩ ይህንን ትምህርት በማንኛዉም ዓይነት መንገድ ለሌላዉ በማዳረስ በአገልግሎቱ ይሳተፉ።

---

ይህ የእግዚአብሔር ልዩ ሦስትነት የሚነገርበት ትምህርት ሚስጢረ ሥላሴ ይባላል። የግዕዝ ቃል ሲሆን ሦስትነት ማለት ነዉ፡፡

በዚህም ሥላሴ የሚለዉ ቃል ሦስትነትን እንጂ አንድነትን አያሳይም፤ ቢሆንም በአብ፥ በወልድ፥ በመንፈስ ቅዱስ አንድነት ያለ ሦስትነት፤ ሦስትነትም ያለ አንድነት አይኖርም፡፡

ሥላሴ ስንት ነዉ ሲባል፣

አንድም ሦስትም እንዲሉ፡፡

መሰረታዊ አስተምሮዉን ባልቀየረ መልኩ ይህንን ትምህርት በማንኛዉም ዓይነት መንገድ ለሌላዉ በማዳረስ በአገልግሎቱ ይሳተፉ።

---

† ሥላሴ ስንል፡

እግዚአብሔር በመለኮቱ አንድ ሲሆን በስም፥ በአካልም ሦስት ነው። አብ፣ወልድ፣መንፈስ ቅዱስ አንድ አምላክ ማለታችን ነዉ፡፡

† ሦስቱም የሥላሴ አካላት፤

- ✓ መለኮታዊ አካላት ናቸው።
- ✓ልዩ አካላት ናቸው።
- ✓እኩልና ዘላለማዊ ባህሪይ አላቸው።
- ✓አንድ ባህርይ፣ አንድም መለኮት አላቸዉ፡፡

መሰረታዊ አስተምሮዉን ባልቀየረ መልኩ ይህንን ትምህርት በማንኛዉም ዓይነት መንገድ ለሌላዉ በማዳረስ በአገልግሎቱ ይሳተፉ።

† በዚህም የተነሳ፡

አብ የራሱ የሆነ መለኮታዊ አካል አለው፤ ወልድም የራሱ የሆነ መለኮታዊ አካል አለው፤ መንፈስ ቅዱስም የራሱ የሆነ መለኮታዊ አካል አለው፡፡

† ሦስቱም አካላት አንድ መለኮት ስላላቸው፤

አብ እግዚአብሔር ነው፡፡

ወልድ እግዚአብሔር ነው፡፡

መንፈስ ቅዱስም እግዚአብሔር ነው፡፡

መሰረታዊ አስተምሮዉን ባልቀየረ መልኩ ይህንን ትምህርት በማንኛዉም ዓይነት መንገድ ለሌላዉ በማዳረስ በአገልግሎቱ ይሳተፉ።

ሦስቱም አካላት አንድ መለኮት ስላላቸው፤

አብ፣ አብ እንጂ ወልድ ወይም መንፈስ ቅዱስ አይደለም፡፡ አይሆንምም፡፡ አይባልምም፡፡

ወልድ፣ ወልድ እንጂ አብ ወይም መንፈስ ቅዱስ አይደለም፡፡ አይሆንምም፡፡ አይባልምም፡፡

መንፈስ ቅዱስም፣ መንፈስ ቅዱስ እንጂ አብ ወይም ወልድ አይደለም፡፡ አይሆንምም፡፡ አይባልምም፡፡

መሰረታዊ አስተምሮዉን ባልቀየረ መልኩ ይህንን ትምህርት በማንኛዉም ዓይነት መንገድ ለሌላዉ በማዳረስ በአገልግሎቱ ይሳተፉ።

ሦስቱም አካላት አንድ መለኮት ስላላቸው፤

አብ፤ ከወልድና ከመንፈስ ቅዱስ ተለይቶ የኖረበት ቅፅበት የለም፡፡ አይኖርምም፡፡

ወልድም፤ ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ ተለይቶ የኖረበት ቅፅበት የለም፡፡ አይኖርምም፡፡

መንፈስ ቅዱስም፤ ከአብና ከወልድ ተለይቶ የኖረበት ቅፅበት የለም፡፡ አይኖርምም፡፡

መሰረታዊ አስተምሮዉን ባልቀየረ መልኩ ይህንን ትምህርት በማንኛዉም ዓይነት መንገድ ለሌላዉ በማዳረስ በአገልግሎቱ ይሳተፉ።

በሥላሴ ሚስጢር አስተምሮ፤ የሥላሴ የስም፣ የአካል፣ የግብር ሦስትነት መለኮቱን አይከፍለዉም፤ የመለኮቱ አንድነትም ሦስትነቱን አይጠቀልለዉም። ሚስጢረ ሥላሴ ማለት ይህ ነዉ!!!

መሰረታዊ አስተምሮዉን ባልቀየረ መልኩ ይህንን ትምህርት በማንኛዉም ዓይነት መንገድ ለሌላዉ በማዳረስ በአገልግሎቱ ይሳተፉ።

# እግዚአብሔር ባልን ጊዜ፤ ስለ አብ፣ ስለ ወልድ፣ ስለ መንፈስ ቅዱስ እንላለን።

# እግዚአብሔር ባልን ጊዜ ስለ ሥላሴ እያሰብን እግዚአብሔር እንላለን።



## መሰረታዊ ጥቅሶች

[ኢሳ$40^{28}$] "እግዚአብሔር የዘላለም አምላክ፥ የምድርም ዳርቻ ፈጣሪ ነው። አይደክምም፥ አይታክትም፥ ማስተዋሉም አይመረመርም። ለደካማ ኃይልን ይሰጣል፥ ጉልበት ለሌለውም ብርታትን ይጨምራል።"

[ኢሳ$40^{12}$፣$44^{24}$] እግዚአብሔር ሁሉን የፈጠረ፥ ሰማያትንም ለብቻዉ የዘረጋ፥ ምድርንም ያጸና፥ ዉኆችን በእፍኙ የሰፈረ፥ ሰማይንም በስንዝር የለካ፥ የምድርንም አፈር በመስፈሪያ ሰብስቦ የያዘ፥ ተራሮችን በሚዛን፥ ኮረብቶችንም በሚዛኖች የሚመዝን ኃያል አምላክ ነዉ።



## መሰረታዊ ጥቅሶች...እግዚአብሔር

እግዚአብሔር ከፍጥረቱ በፊት ነበር። እርሱ ፍጥረቱን ለክብሩ ፈጥሯል። በሰማይም ፣ በምድርም ያሉት ሰውም በርሱ ለርሱ ተፈጥረዋል። ፍጥረቱንም በሥርዓቱ የሚመራዉ እራሱ ነው። በዚህም "አዶናይ" ይባላል።

[ኢሳ$43^{11-13}$፣$45^{24}$፣$46^{9}$] እግዚአብሔር ብርቱ ፥ ሁሉን ማድረግ የሚቻለው፥ የሃያላን ሁሉ ሃያል፥ መጀመሪያና መጨረሻ ፥ ጥንትና ፍጻሜም የሌለው፤ በራሱ የሚኖር አምላክ ነው። እርሱ ፊተኛም ነው ፤ እርሱኋለኛም ነው።



## ማስታወሻ...

† እስካሁን ባየነዉ እግዚአብሔር፡

- ዙፋኑ ከጥንት ጀምሮ የተዘጋጀ ነው፤ እርሱም ከዘላለም ነው። [መዝ$93^{2}$]
- ስራው እጅግ ትልቅ ፥ ሃሳቡም እጅግ ጥልቅ ነው። [መዝ$92^{5}$]
- ባለጠግነትና ጥበቡ ዕዉቀቱም እጅግ ጥልቅ፥ ፍርዱም የማይመረመር ፥ ለመንገዱም ፍለጋ የሌለዉ አምላክ ነዉ።
- የሁሉም ጥበብ መገኛ ፤ የዕውቀትም ሁሉ ምንጭ ነው። ........የሚሆነውን ከመሆኑ አስቀድሞ ያውቃል!
- ሁሉን ያደርጋል ፥ የሚያቅተው የለም። .......ሃሳቡንም የሚከለክለው የለም!
- ሁሉን ፈጥሯል ፥ሁሉንም ይመራል ። በፈጠራቸው ፍጥረቱ ለመስራት አስቀድሞ ያዘጋጀው ዓላማ አለው። [ኤፌ$2^{10}$]
- ያለ እርሱ ፍቃድና ዕውቀት ምንም አይሆንም ። አይደረግምም። [ማቴ$10^{29-30}$]

## † እግዚአብሔር መንፈስ ነውና በዓይን አይታይም።

[ዘጸ33[20]] ፦እግዚአብሔርን ማንም አላየውም። ሰው አይቶት አይድንምና!

[ዮሃ1[18]] ” መቼም ቢሆን እግዚአብሔርን ያየው አንድ ስንኳ የለም በአባቱ እቅፍ ያለ አንድ ልጁ እርሱ ተረከው።”

- በክብር የሚስተካከለው ልጁ ፍቅሩን ፥ ምህረቱን ፥ ኃይሉንም ገልጦልናል።



## መሰረታዊ ጥቅሶች

[ዮሃ17[3]] “እውነተኛ አምላክ ብቻ የሆንህ አንተን የላክኸውንም ኢየሱስ ክርስቶስን ያውቁ ዘንድ ይህች የዘላለም ሕይወት ናት።”

[ዕብ1[1-4]] “ከጥንት ጀምሮ እግዚአብሔር በብዙ ዓይነትና በብዙ ጎዳና ለአባቶቻችን በነቢያት ተናግሮ፥ ሁሉን ወራሽ ባደረገው ደግሞም ዓለማትን በፈጠረበት በልጁ በዚህ ዘመን መጨረሻ ለእኛ ተናገረን፤ እርሱም የክብሩ መንጸባረቅና የባሕርዩ ምሳሌ ሆኖ፥ ሁሉን በስልጣኑ ቃል እየደገፈ፥ ኃጢአታችንን በራሱ ካነጻ በኋላ በሰማያት በግርማው ቀኝ ተቀመጠ፤ ከመላእክት ይልቅ እጅግ የሚበልጥ ስምን በወረሰ መጠን እንዲሁ ከእነርሱ አብዝቶ ይበልጣል።”

[1ዮሃ5[10-12]] “በእግዚአብሔር ልጅ የሚያምን በነፍሱ ምስክር አለው፤ በእግዚአብሔር የማያምን እግዚአብሔር ስለ ልጁ የመሰከረውን ምስክር ስላላመነ ሐሰተኛ አድርጎታል። እግዚአብሔርም የዘላለምን ሕይወት እንደ ሰጠን ይህም ሕይወት በልጁ እንዳለ ምስክሩ ይህ ነው። ልጁ ያለው ሕይወት አለው፤ የእግዚአብሔር ልጅ የሌለው ሕይወት የለውም።”

[1ዮሃ5[20]] “የእግዚአብሔርም ልጅ እንደ መጣ፥ እውነተኛም የሆነውን እናውቅ ዘንድ ልቡናን እንደ ሰጠን እናውቃለን፤ እውነተኛም በሆነው በእርሱ አለን፥ እርሱም ልጁ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። እርሱ እውነተኛ አምላክና የዘላለም ሕይወት ነው።”

መሰረታዊ አስተምሮዉን ባልቀየረ መልኩ ይህንን ትምህርት በማንኛዉም ዓይነት መንገድ ለሌላዉ በማዳረስ በአገልግሎቱ ይሳተፉ።

[ሮሜ9[4-5]]

“እነርሱ እስራኤላውያን ናቸውና፥ ልጅነትና ክብር ኪዳንም የሕግም መሰጠት የመቅደስም ሥርዓት የተስፋውም ቃላት ለእነርሱ ናቸውና፤ አባቶችም ለእነርሱ ናቸውና፤ ከእነርሱም ክርስቶስ በሥጋ መጣ፥ እርሱም ከሁሉ በላይ ሆኖ ለዘላለም የተባረከ አምላክ ነው፤ አሜን።”

የሚለዉና

[ዮሃ1[11-12]]

“የእርሱ ወደ ሆነው መጣ፥ የገዛ ወገኖቹም አልተቀበሉትም። ለተቀበሉት ሁሉ ግን፥ በስሙ ለሚያምኑት ለእነርሱ የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ ሥልጣንን ሰጣቸው።”

ትምህርት የሓዲስ ኪዳን ማዕከላዊ ሃሳብ ሆኖ እናገኛዋለን ።

ጌታ ራሱ “እኔ መንገድና እውነት ሕይወትም ነኝ፤ በእኔ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም።” [ዮሃ14[6]] ያለው፥ ስለዚህ ምክንያት ነዉ።

መሰረታዊ አስተምሮዉን ባልቀየረ መልኩ ይህንን ትምህርት በማንኛዉም ዓይነት መንገድ ለሌላዉ በማዳረስ በአገልግሎቱ ይሳተፉ።




መሰረታዊ አስተምሮዉን ባልቀየረ መልኩ ይህንን ትምህርት በማንኛዉም ዓይነት መንገድ ለሌላዉ በማዳረስ በአገልግሎቱ ይሳተፉ።

ከአዳም የተላለፈብኝን ኃጢአት ያስወግድ ዘንድ፥ ከብፀዕት፥ንጽሕት፥ ድንግል ማሪያም ያለ አባት ተወልዶ ፥ በሥጋ የተገለጠዉ ኢየሱስ፤ እርሱ የእግዚአብሔር መልክ ያለዉ፤ ራሱም እግዚአብሔር የሆነ፥ የክብሩ መንጸባረቅ ነዉ። ከሁሉም በላይ ሆኖ ለዘላለም የተባረከ አምላክ የሆነው እርሱ ፤ ወደ እግዚአብሔር የምቀርብበት ብቸኛ መንገዴ ነዉ። ብሎ ማመን ነዉ።

መሰረታዊ አስተምሮዉን ባልቀየረ መልኩ ይህንን ትምህርት በማንኛዉም ዓይነት መንገድ ለሌላዉ በማዳረስ በአገልግሎቱ ይሳተፉ።

በዚህም እግዚአብሔር ምን እንደሚመስል ለመረዳት ከፈለግን ዉድ ልጁን ኢየሱስ ክርስቶስን በግል ማወቅና ማጥናት ብቻ እንዳለብን እናያለን። የመለኮቱ ሙላት በርሱ ለይ ተገልጦ ይታያልና!

መሰረታዊ አስተምሮዉን ባልቀየረ መልኩ ይህንን ትምህርት በማንኛዉም ዓይነት መንገድ ለሌላዉ በማዳረስ በአገልግሎቱ ይሳተፉ።